# ቀኑ ሳይመሽ፥ ብርሃን ሳይሸሽ

**ጌታቸው ኃይሌ**

ከሳምንታት በፊት የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባርና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከአምስት ወር በኋላ ስለሚካሄደው የ2002 ዓ. ም. ምርጫ "የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ሥነ ምግባር ደምብ እና በደምቡ ማስፈጸሚያ መምሪያ ላይ ባደረጉት ድርድር ስምምነት የተደረሰበት ሰነድ" የሚሉት አንድ የቅድመ ሁኔታ ውል እንደተዋዋሉ እናስታውሳለን። ውሉን በእርግጥ ለማክበር ይሁን ወይም ለማስመሰል ባልተረጋገጠ ምክንያት ግምባሩ አንዳንድ ቀና ነገር እንዳደረገ የመላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (የመኢአድ) ሹማምንት ይናገራሉ። ለምሳሌ፥ መኢአድ ባሕር ዳርና መቀሌ ላይ ያደረጋቸው ሕዝባዊ ስብሰባዎች የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር በሚቈጣጠረው የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን በቅንጭብም ቢሆን ለሕዝብ ተነግረዋል። ሁለተኛም፥ ታኅሣሥ 23 ቀን 2002 ዓ. ም. በወጣው *የአንድነት* ጋዜጣ ላይ የመኢአድ መሪዎች ለሕዝብ በሰጡት መግለጫ ውስጥ ድርጅቱን ለመምረጥ በመወሰንህና በመዘጋጀትህ "በሥራህም ሆነ በጥቅምህ ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ ወይም ጉዳት እንደማይደርስብህ በሙሉ ልብ እናረጋግጥልሃለን" ብለዋል።

መቸም "እባብ ያየ ያንኑ እባብ ልጥ ለብሶ ቢያይ በራ" ነውና በግንቦት 97 ዓ. ም. ለጥቂት ቀናት የታየው የነፃነት ብልጭታ ወዲያው ውድም ስላለ ያሁኑን መልካም ገጽታ ዘላቂነት ይኖረዋል ብሎ መገመት ያስቸግራል። ሆኖም የተስፋው ጮራ ይቺን አጭር ጽሑፍ ለመጻፍ ምክንያት ሆኖኛል። የጽሑፉ ዓላማ ይህ አሁን ብልጭ ያለው የንግግር ነፃነት ብርሃን እንደተለመደው ወደመጣበት እንደሚመለስና ቀኑ እንደሚጨልም ገምቶ፥ አሁኑኑ በጥድፊያ መሠረታዊ እርምጃዎችን መውሰድ እንደሚያስፈልግ የታወቀውን ነገር በእግረ ሕሊና ቆሜ ለሚመለከታቸው ሁሉ ማስታወስ ነው።

**መሠረታዊ እርምጃ፤**

ብልጭ ያለው ተስፋው ባለፍሬ ቢሆንም ባይሆንም፥ ቤታቸው እስኪፈርስ፥ ደማቸው እስኪፈስ፥ ታግለው ለዚህ ተስፋ ያበቁንን ጀግኖቻችንን ከሁሉ አስቀድሜ ነወር እላለሁ። ኢትዮጵያ ሁል ጊዜም የጀግኖች እናት መሆኗን አስመስክረዋል። ከዚያ ቀጥዬ ሥነ ምግባሩን ወደ እውነተኛነት ለማቅረብ እነወይዘሮ ብርቱካን ሚዴቅሳና ሌሎችም የፖለቲካ እስረኞች ባስቸኳይ ተፈትተው ለምርጫው እንዲዘጋጁ ሁሉም ድምፁን እንዲያሰማ እለምናለሁ።

አሁን እንግዴህ ተቃዋሚ ቡድኖች በጥድፊያ ሊራመዱት ይገባል የምለውን መሠረታዊ እርምጃ ልግለጽ። እሱውም **አገር አድን ኅብረት** መፍጠር ነው። ጽሑፌ የሚማፀነው በጠቅላላ መላ የኢትዮጵያን ሕዝብ፥ በተለየም አምላክ የመሪነትና የተሰሚነት ሀብት የሰጣቸውን ነው። መልእክቱ ለፓርቲዎች፥ ለፓርቲ መሪዎች፥ ለጎበዝ አለቆች ይድረስልኝ። በሌላ አነጋገር፥ የጽሑፌ ፍሬ ነገር ተባብረን ራሳችንንና ልጆቻችንን **ከሀገር አልባነትና ከጥገኝነት** እናውጣ የሚል ነው። የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር በሥልጣን ላይ ከቆየ **ሀገር አልባነትና ጥገኝነት** አይቀርልንም። መልክቱ፥ "አፋችንን ከዘጋን በሰላም ወጥተን በሰላም እንመለሳለን፤ ምን ጎደለብን? ጥንትስ ቢሆን ከዚህ የበለጠ ምን ነፃነት ኖሮን ያውቃል?" ለሚሉትም ጭምር ነው። በማቀርበው ጥሪ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንዲተባበሩኝና ኀላፊዎቹ ጥሪውን እንዲሰሙ ከባድ ተጽዕኖ እንዲያደርጉባቸው በአክብሮት እለምናለሁ።

እስቲ እናስበው፤ በፊት ድኾች ነበርን፤ ግን "ኢትዮጵያውያን ነኝ" ስንል አንገታችንን በኩራት ቀና አድርገን ነበር። ሕዝቡ "ከድኽነት ለመውጣት የምንችለው የጭቆና አገዛዝን ስናስቀር ነው" ብሎ ተነሣ። የጭቆና አገዛዝን ለማስወገድ ብዙ ደም ፈሰሰ። ጭቆና ግን

እንኳን ሊወገድ ድክመትም አልደረሰበት። እንዲያውም ባዝራ ፈረስ እየጋለበ በተጠናከረ ኀይል መጥቶ፥ ብሔራዊ ኩራታችንንም ወሰደብን። በአሁኑ ሰዓት "ከየት ነህ?" የሚለውን ጥያቄ የሚፈሩ ኢትዮጵያውያን ጥቂቶች አይደሉም። አይፈረድባቸውም፤ የውዳቂ ሀገር ሰዎች ሆነናል።

በፊት ባለታሪክ ነበርን፤ ከጥቂቶቹ የጥንት አገሮች የምትቆጠር አገር ነበረችን። ታሪክ አልባ ሊያደርጉን የጥንቱን መጻሕፍት እያቃጠሉ ሌላ መጽሐፍ ጻፉልን።

ሙከራው አልሆን ቢላቸው በራሷ በሀገሪቱ ላይ ዘመቱባት። "ብሔረሰብ ሁሉ ከፈለገ የሰፈረበትን ክፍል ሀገር ይዞ መሄድ ይችላል" የሚል አፍራሽ ዓዋጅ ዐወጁባት። ዓዋጁን በሰሜን በኩል ሞከሩት። ሙከራው ኤርትራውያንን ባይጠቅማቸውም ኢትዮጵያን ለማፍረስ ጠላቶቻችንን ጠቀማቸው።

የፈለገ የጎረቤት ሀገር የኢትዮጵያን መሬት ገምሶ ለመውሰድ እንዲችል መንገዱን አመቻቹለት፤ በሱዳን በኩል ሞከሩት፤ የጎረቤት መሬት መውሰድ ለሱዳን ዘላቂ ጥቅም እንደማያስገኝላት ቢታወቅም ኢትዮጵያን ለማፍረስ ጠላቶቻችንን ጠቀማቸው።

ፓኪስታን፥ ህንድ፥ የሳውድ ዐረቢያ፥ ግብጽ ጉርብትና ስለሌላቸው መሬት ገምሶ መስጠት ሳያመች ጊዜ ማህል አገር ገብተው የፈለጉትን ያህል በዶለር እየለኩ እንዲወስዱ ተጋበዙ። አገሪቱን የሚገዟት ሄደው እነሆ የሚሸጧት መጡባት።

"የተሸጠው ያደረው (ያልታረሰው) ሰፊው መሬት ነው" ይሉናል። ኢትዮጵያ ከአሜሪካ፥ ከካናዳ፥ ከብራዚል፥ ከአርጀንቲና የሰፋ ያልታረሰ መሬት የላትም። የትም ሄዶ ያልታረሰ መሬት መግዛት ካስኬደ ለምን እዚያ ሄደው አይገዙም? "ለሀገሪቷ የውጪ ሀብት ለማምጣት፥ ሰፋፊ እርሻ ያስፈልጋታል" ይሉናል። አገሪቷ የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባርና የውጪ ሀገር የግል ሀብት ሆነች እንጂ መች የውጪ ሀብት አገኘች? ሰፋፊ እርሻ ሀገር ከጠቀመ ለምን ሕዝብና መንግሥት የሚመጥነውን ያህል እየለኩ ሰፋፊ እርሻ አያርሱትም? የውጪ ሀብት የሚገኘው እንደ የመኪና፥ የኮምፒዩተር፥ የልብሳልብስ፥ ወዘተ ማምረቻ ፋብሪካ ቢያቋቁሙ ነበር እንጂ ዋናውን የሕዝብ መተዳደሪያ የሆነውን የእርሻና የከብት ርቢ ሥራ ሲወስዱበት አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ እጁን የፊጥኝ ታስሮ ነው እንጂ ቢለቀቅ በቴክኖሎጂና የፋብሪካ ምርት በማምረት የሚወዳደረው ከጃፓንና ከደቡብ ኮሪያ ጋር ነበር። የሚጠራጠር ካለ፥ ኢትዮጵያውያን በተሰደዱበት አህጉር ሁሉ የሚሠሩትን ተአምር ማንበብ ይችላል።

አሁን ደግሞ "የዓባይን ልጅ ውሐ ጠማው" የሚለው አነጋገር ትንግርት ሆኖ እነ አቶ መለስ ዓባይንም ለሱዳንና ለግብጽ ሸጡት። ግብጽና ሱዳን በምድራቸው ላይ የሚፈስሰውን ውሐ በ1959 ዓ. እ. በተፈራረሙት ውል ተከፋፍለውት ነበር። በሀገራቸው ምድር ላይ የሚፈስሰውን ውሐ በምንም ዓይነት ውል ቢከፋፈሉት ኢትዮጵያን አይገዳትም ነበር፤ አሁን ያ ውል ከጣና ባሕር ጀምሮ ኢትዮጵያ ምድር ላይ የሚፈስሰውን፥ ማለት ከኢትዮጵያ ያልወጣውንም ውሐ፥ እንዲጨምር የእነ አቶ መለስን መልካም ፈቃድ ጠይቀው መልካሙን ፈቃድ በምስጢር አገኙ። ምስጢርነቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንጂ ግብጾችማ በአደባባይ ለአቶ መለስ ረጅም እድሜ ለምነዋል። እኛስ? እኛማ የአቶ መለስንና የግብር አበሮቹን የፖለቲካ እድሜ ለማሳጠር ቈርጠን መነሣት አለብን።

ኀላፊነቱ የማን ነው?

የሚሠራውን ብሔራዊ ወንጀል ለማቆም ኀላፊነቱ የኢትዮጵያውያን ሁሉና የነሱ ብቻ ነው። ወንጀሉ የሚቀረቀረው፥ አገሪቱን "አገሬ፥ የልጆቼና የልጅ ልጆቼ አገር ናት" የሚላት ሁሉ መሆኑ ግልጽ ነው። ወያኔዎቹ ይኸን ስለሚያውቁ፥ ተቈርቋሪው እየተመረጠ አገር ጥሎ

እንዲሄድ አስጨንቀው ይዘውታል። ከወጣም እንዳይመለስ ቀደም ብለው የሞት ቅጣት የሚያስፈርድ ክስ መሥርተው ይጠብቁታል። ስለዚህ መልክቴ በመጀመሪያ ደረጃ የሚመለከተው ጨክኖ አገሩን የሙጥኝ ያለውን ነባሩን ኢትዮጵያዊ ነው፤ እውጪ ያለውም በሚቻለው መንገድ ሁሉ ይረዳል። ሆኖም አቅሙ ቁሳዊ እርዳታና መንፈሳዊ ድጋፍ በመስጠት የተወሰነ ነው። ድል የሚያስገኘው የፊት ለፊቱ ግፊት ግን ነባሩ የሚሸከመው መስቀል ሆኗል።

በአሁኑ ሰዓት አገራችን ኢትዮጵያ (1) አምላኳን፥ (2) በሀገር ውስጥ ያሉ ኢትዮጵያውያንን፥ (3) ፓርቲዎችን፥ (4) የፓርቲ መሪዎችን፥ (5) የኅበዝ አለቆችን መማፀን የግድ ሆኖባታል። የደረሰባት አደጋ ሁሉንም የሚያስተባብር መቅሠፍት ነው። መቅሠፍቱ ያጠፋናል፤ ትንሽ ብንተርፍም የተረፍነውን የሌሎች ተገዢ አድርጎ ያስቀረናል። አደጋው ካሁን በፊት ታይቶ የማይታወቅ ዓይነት ስለሆነ፥ አባቶቻችን የዘመናቸውን ጠላት በአሸነፉበት መንገድ የሚሸነፍ አይደለም። የዱሮው ጠላት የውጪ አገር ሰው ነበር፤ የዛሬው ጠላት ዘመድ መስሎ ከማህላችን ተቀምጧል። የዱሮው ጠላት መሸነፊያው ነፍጥ ብቻ ነበር፤ የዛሬውን ጠላት የምናሸንፈው በሰላማዊ ዐመፅ ጭምር ነው።

ለጠላት የልብ ልብ የሰጡትና ዋና ኀይል የሆኑት እሱ ቢባረር ጥቅማቸው የሚቀርባቸው የሚመስላቸው ወገኖቻችን ናቸው። እሱ ቢሄድ፥ እሱ ከሚሰጣቸው የበለጠ ጥቅም እንደሚያገኙ ልብ አላሉትም። የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባርን አገዛዝ ለመንቀል የሚፈልገው ለሁሉም እኩል ጥቅም የሚያስገኝለትን አስተዳደር ለመዘርጋት እንጂ በሌላ ጨቋኝ፥ ወይም ለጎሳው በሚያዳላ በሌላ ጎሳ አገዛዝ ለመተካት አይደለም። የራስን መብት ከትግሬ ወያኔዎች እጅ በችሮታ ከመጠበቅ መብትን ማስከበር ይበልጣል፤ ያኮራል። የራሳችንን መብት የሚመጸውቱንን አባርረን መብታችንን እናስመልስ።

**አንድዬ ስልት፤**

***የኢትዮጵያ ሕዝብ መብቱን የሚጠብቅለትና ሁሉንም እኩል የሚጠቅም አስተዳደር ለመዘርጋት የሚችለው የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባርን አገዛዝ የሚቃወሙና በዲሞክራሲ የሚያምኑ ሁሉ ለአንዳፍታ ሲተባበሩ ብቻ ነው።*** ድርጅቶች በዚህ ዓላማ ካልተባበሩ ቁም ነገሩ ቀርቶ ፖለቲካ ተቺዎች ሆነው ይቀራሉ እንጂ ሕዝብ የሚጠቅም አንዲት ቅንጣት ለውጥ አያመጡም። የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ በዲሞክራሲና በነፃነት ኑሮ እንደሚያምኑ አያጠራጥርም። ምክንያቱም፥ ነፃነት የማይናፍቀው የፖለቲካ ፓርቲ አያቋቁምም። ስለዚህ ኅብረቱን እንዲመሠርቱ የምማፀነው ፓርቲዎቹን ሁሉ ነው። በአሁኑ ሰዓት እንዲህ ያለ ሰፊ ጥሪ ማቅረብ ሞኝነት ይመስላል። ሞኝነትስ ሌላ አማራጭ እንደሌለን አለመገንዘብ ነው።

እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ የተመሠረተው በማኒፌስቶው ያሰፈረውን ብሶት ይዞ ነው። ግን የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር በአገዛዝ እያለ፥ ማንኛውም ፓርቲ ለተመሠረተበት ብሶት መፍትሔ አያገኝም። ይኸንን የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር መሪ “የኛና የሌሎቹ ዓላማ የተለያየ ነው፤ በሥራ ላይ የሚውለው ወይ የኛ ወይ የነሱ ፍላጎት ነው” ብሎ በማያወላውል ቋንቋ ነግሮናል። የሱ ፍላጎት አገር መሸጥ ነው፤ የሌሎቹ ፓርቲዎች ዓላማ ለብሶታቸው መፍትሔ መፈለግ ነው።

በዚህ ከተስማማን ኅብረቱ በጥብቅ ይፈለጋል እንጂ አይፈራም። ኅብረት የሚያስቸግረው “የብሶታችን መፍትሔው መገንጠል ነው” ከሚሉት ጋር ነው እንጂ “ብሶታችን በኢትዮጵያ አንድነት ውስጥ ይፈታል” ከሚሉት ጋር አይደለም። ኢትዮጵያን “አገሬ ናት” የሚል ሁሉ ለብሶቱ የሌሎቹን ኢትዮጵያውያን መብት የማይነካ መፍትሔ መፈለግ የማይገሠሥ መብቱ ነው። ይኸንን ፓርቲዎች ሁሉ ማወቅና ማክበር አለባቸው። አገሪቱን አገሬ የሚልና

በዲሞክራሲ አስተዳደር የሚያምን ሁሉ የሕዝቧን ሰላምና ብልጽግና ይፈልጋል፡፡ አገር ለማጥፋት የሚፈልግ እንደትግሬ ወያኔዎች የነፃ አውጪ ግምባር (Liberation Front) ያቋቁማል እንጂ የፖለቲካ ፓርቲ አያቋቁምም፡፡ የፖለቲካ ፓርቲ የሚያቋቁመውን ሁሉ እናከብራለን፤ ለመብቱም እንከራከርለታለን፡፡

እንደ የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር ያሉ የነፃ አውጪ ግምባሮችን ግን ልንፈራቸው ይገባል፡፡ የእነሱ አደገኛ ዓላማ ሰላማዊ ለውጥ የሚፈልጉ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ሁሉ ለማስተባበር በቂ እና ዋና ምክንያት ነው፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎቻችን የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር በሀገሪቱ ላይ የቱን ያህል ጉዳት እንዳመጣ አይተዋል፡፡ ሀገር ለመጉዳት ሌሎቹም ግምባሮች ከትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር አያንሱም፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የግምባሮቹ ጉዳት ከተሰማቸው፥ ያላንዳች ማወላወል ይተባበሩ ይመስለኛል፡፡ አገሪቷን ከትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር አገዛዝ ነፃ ለማውጣትና በጋራ ለማደስ፥ ፓርቲዎች ሁሉ “የዘር ነህ”፥ “የቀኝ ክንፍ ነህ”፥ “የግራ ክንፍ ነህ” ሳይባባሉ አብረው መነሣት አለባቸው፡፡ የአንድ ሀገር ዕድል በጠቅላላው ሕዝብ ምኞትና ፈቃድ እንጂ በአንድ ነፃ አውጪ ግምባር ወይም የፖለቲካ ፓርቲ መወሰን የለበትም፡፡

ከባድ ሐሳብ፤

የኢትዮጵያ አንድነት በካርታዋ ብቻ ሳይሆን በሕዝቡም መደበላለቅ ጭምር መሆኑን ዕውር እንኳን በዳበሳ የሚያውቀው ነው፡፡ በዲሞክራሲ ካመንንም፥ ሀገሪቷ የግራና የቀኝ ክንፍ እንደሚኖራት ማመንና መቀበል አለብን፡፡ ሆኖም ሀገራዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች “በዘር ከተደራጁ ፓርቲዎች ጋር ኅብረት ይፍጠሩ፥ የቀኝ ክንፍና የግራ ክንፍ አብረው ይሰለፉ” የምለው ሐሳብ ከባድ ይመስላል፡፡ ግን ወሳኙ የኅብረቱ ዓላማ ነው፡፡ የኅብረቱ ዓላማ ተሚሙቶ ወያኔዎቹን ለማሸነፍ ነው፤ ጊዜያዊ ነው፡፡ እርግጥ በወያኔዎች ዓይን፥ የሚቀጥለው ምርጫ የአሸነፊ ፓርቲ መንግሥት እንዲያቋቁም ነው፤ ይሁንላቸው፤ ይመኑበት፡፡ በተቃዋሚዎቹ ዓይን ግን ወያኔዎች በሥልጣን ላይ እስካሉ ድረስ ይኸ የሕልም ሩጫ ነው፡፡ ስለዚህ የቃዋሚ ፓርቲዎች የ2002ን ምርጫ ዲሞክራሲን የሚመሠርት ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት ለማቋቋም መተባበሪያ እንዲያደርጉት ሐሳብ ላቅርብ፡፡

ፓርቲዎች ተባብረው የሚያቋቁሙት የሽግግር መንግሥት የኢትዮጵያን ብዙ ችግሮች የሚፈታ ኢትዮጵያዊ ዲሞክራሲን ይቀይሳል፡፡ ከትላልቆቹም ከትናንሾቹም ብሔረሰቦች የሚነሡትን ብሶቶች የራሱ ጉዳይ አድርጎ መፍትሔ ይፈልግላቸዋል፡፡ ይህን ለማድረግ የሚቻለው የፖለቲካው መስክ ሲስተካከል ብቻ ነው፡፡ መስኩ የሚስተካከለው ደግሞ ኮረኮንቹ የወያኔ ግዛት ሲጠረግ ነው፡፡ ቀርቧል የተባለውን የምርጫ ዕድል ተባብረን በወያኔዎች ላይ ለመነሣት እንጠቀምበት፡፡ የውድድር ዘመን የደረሰ መስሎን እስከዛሬ በፓርቲ ለመወዳደር የሞከርነው ወያኔዎች አሳስተውን ነው፤ ዘመኑ አልደረሰም፡፡ ዘመኑ የሚደርሰው ወያኔዎች ከሥልጣን ወርደው፥ ወያኔዎችን ጨምሮ ሁሉም እኩል ለመወዳደር መስኩ ሲስስተካከል ነው፡፡ ኢትዮጵያ የሁሉም አገር መሆኗን ከአመንን፥ የዘር፥ የቀኝ ክንፍ፥ የግራ ክንፍ የሆኑት ሁሉ በጥርጊያው መተባበር አለባቸው፡፡ በሀገር ጉዳይ ከነዚህ ውስጥ አንዱ ከሌላው የበለጠ ወይም ያነሰ መብት ያለው የለውም፡፡ አለው የሚል ሰው ካለ በፖለቲካው መስክ ቦታ የለውም፡፡

ኅብረት እንዲፈጠር የማሳስበው የሁሉንም ብሶት ጥሎ የአንዱን ብሶት ብቻ ለማስተናገድ ሳይሆን፥ ብሶቶችን ሁሉ ለማስወገድ እንዲመች ደንቃራውን ከመንገዳችን ላይ ለማንሣት ነው፡፡ ለሚቀጥለው ምርጫ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት (መኢአድ) እና በመድረክ የተሰባሰቡት ፓርቲዎች አሁኑኑ መጠራራትና ኅብረት ፈጥረው በትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር ላይ ሰላማዊ ዘመቻ መዝመት አለባቸው፡፡ ዕድሉ አሁን ነው--ሳይመሽ፥ ብርሃን ሳይሸሽ፤ አቶ መለስ የባሰውን ነገር ሳያበላሽ፡፡ መንግሥት ለማቋቋም የሚደረገው ውድድር

ከዚያ በኋላ ይመጣል። ፓርቲዎች ሁሉ አብረው ካልታገሉ አማራጩ የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባርና የኢትዮጵያ መሬት የተሸጠላቸው ሕዝቦች ታዛዥ ሆኖ መቅረት ነው።

የብሔረሰብ ፖለቲካ ዘረኝነት ስለሆነ ለምንም ዓላማ በዘር ከተደራጁ ፓርቲዎች ጋር አንድነት መፍጠር ይከብድ ይሆናል፤ እርግጥ ነው። የፖለቲካ ድርሰቶቼን ያነበበ ሁሉ እኔም በዚህ እንደምስማማ ያውቃል። ዘረኝነት አገር ይጎዳል፤ ሕዝብ ያለያያል። እቋንቋ ላይ የተመሠረቱ መንግሥታት አንድ የጋራ ቋንቋ ከሌላቸው፥ በፌዴሬሽንም ሆነ በኮንፌዴሬሽን የጠበቀ አንድነት ሊፈጥሩ አይችሉም። ግን የብሔረሰብ ፖለቲካ የሚጎዳው ሁሉንም ነው። በብሔረሰብ የተደራጁትንም አይምራቸውም። ሕዝቡ የዕውቀት ደረጃው እየዳበረና እየተስተካከለ ሲሄድ እንዲህ ያሉ ፓርቲዎችን ያመነምናቸዋል፤ አለዚያም ኮከስ (caucus) ያደርጋቸዋል። ነፃነቱ ሲገኝ ተከታይ እንዲያጡ በነፃና በሰላም መታገል እንጂ በዲሞክራሲ መንገድ ላይ ያለውን ደንቃራ ለማጥፋት ከእነሱ ጋር አንተባበርም አይባልም፤ ኢትዮጵያዊነታቸውን መካድ ይሆናል።

ሁለተኛም፥ በመድረክ ውስጥ በተሰባሰቡት የብሔረሰብ ድርጅቶችና በኢሕአዴግ ውስጥ ባሉት የብሔረሰብ ድርጅቶች መካከል መሠረታዊ ልዩነት አለ፤ የኢሕአዴግ ድርጅቶች የትግሬ ወያኔዎች ፍጡሮች ናቸው፤ ፈጣሪያቸው የፈለገውን ያዝዛቸዋል፤ እነሱም "እግዚኦ መሐረን" እያሉ ለፈጣሪያቸው ይታዘዛሉ። ሀገር ከመጉዳት አይመለሱም፤ ሀገርን መጉዳት ራስን መጉዳት መሆኑን አያውቁም። በመድረክ ውስጥ ያሉት ድርጅቶች ግን ራሳቸውን የፈጠሩ ስለሆኑ የራሳቸው ጌቶች ናቸው፤ ኢትዮጵያን ሀገራቸውን የሚጎዳ ሥራ እንዲሠሩ የሚያዝዛቸው የለም። ሀገርን መጉዳት ራስን መጉዳት መሆኑን ያውቃሉ። አቅሙም የራሳቸው ነው፤ እሱም ለማስቸገር የሚያስችል ከሌሎቹ ኅብረት ፈጣሪዎች የበለጠ አቅም አይደለም።

በኢትዮጵያዊነት የተመሠረቱ ድርጅቶችና በብሔረሰብ መሠረት በተቋቋሙ ድርጅቶች መካከል ያለው አለመግባባት ለትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጭ ግምባር (ለወያኔ) ትልቅ ኀይልና የሕይወት እስትንፋስ ሆኖታል። ሁለቱ ሳይስማሙም እንዲኖሩ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል። ሕይወቱ አንዱን በሌላው በማስፈራራት ስለሆነ፥ ኅብረት በመፍጠር ማስፈራሪያውን መንሣት ለሀገር ማሰብ ነው። በብሔረሰብ መሠረት የተቋቋሙ ድርጅቶችም በኢትዮጵያዊነት ከተመሠረቱ ድርጅቶች ጋር ለዲሞክራሲ አብሮ ለመታገል የማይፈልጉበት በቂ ምክንያት አይኖርም። ብሶታቸውን በዲሞክራሲ ከመፍታት ሌላ ምን ይፈልጋሉ? ከዚህ የተለየ ነገር ከፈለጉ ትግላቸው ለሀገር ነፃነት መሆኑ ያጠራጥራል።

አንዳንድ ድርጅቶች ሀገር ገብተው በዚህ ሀገራዊ ትግል እንዳይሚሟቱ የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር መብቱን እንደነሣቸው ይታወሳል። እነሱም በልዩ ልዩ ዘዴ ከኅብረቱ ገብተው መታገል አለባቸው። አባሎቹ መንቀሳቀስ በተፈቀደላቸው ፓርቲዎች ውስጥ በግለ ሰብ ደረጃ እየገቡ ግዴታቸውን እንደሚፈጽሙ ተስፋ አደርጋለሁ። ኢትዮጵያ የነሱም ነች፤ የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር ወድቆ ነፃ ብንሆን ድሉ የነሱም ነው።

**አፍ መዝጋት ያስጠይቃል፤**

"አፋችንን ከዘጋን በሰላም ወጥተን በሰላም እንመለሳለን፤ ምን ጎደለብን? ጥንትስ ቢሆን ከዚህ የበለጠ ምን ነፃነት ኖሮን ያውቃል?" የሚሉ ካሉ፥ ያላዩት አገር የማይናፍቅ ቢሆንባቸው ነውና የሙሉ ነፃነትን ጣዕም ማስተማር የፓርቲዎች ግዴታ ነው። ሙሉ ነፃነት ሐሳብን ያለፍርሃት መግለጽን ይጨምራል። እነ አፈ-ዝግ አህያ፥ በቅሎ፥ ፈረስ በሰላም ወጥተው በሰላም ይመለሳሉ፤ ጅብ እንዳይበላቸውም እረኛ ይቀጠርላቸዋል። ኑሯቸው ግን በባርነት ነው። አምላክ ከፍጡሮቹ ሁሉ ለይቶ ለሰው ልጅ አንደበት የሰጠው እንደሌሎቹ ፍጡራን አፉን እንዳይዘጋ ነው። አንደበት መክሊት ነው። ጀግኖች በተሰጣቸው አንደበት የሠሩበትን በፉከራና በኩራት ሲያስመሰክሩ፥ ያልሠሩበት "በተሰጠህ መክሊት ምን አደረክበት?"

ተብለው በአምላክና በሕዝብ ዘንድ ይጠየቃሉ፡፡ አገር ስትጠፋ እያየ ፈርቶ በመክሊቱ ያልሠራበት መልሱን ያዝዘጋጅ፡፡ የሰው ልጅ ለነፃነቱ በአንደበት፥ በብዕር፥ በነፍጥ የሚታገለው ነፃነት አምሳያ ስለሌላት ነው፡፡

**ነፃነት አምሳያ የላትም፤**

ነፃ ስንሆን፥ ከማንኛውም ጭቆና ነፃ እንሆናለን፤

ነፃ ስንሆን፥ የፈለግነውን ጽፈንና ተናግረን እናድራለን፤

ነፃ ስንሆን፥ የፈለግነውን ቅን ሥራ ሠርተን ፍሬውን የራሳችን እናደርጋለን፤

ነፃ ስንሆን፥ በዓለም ፊት ራቁታችንን መቆም ይቀርልንና ክብር እንጐናጸፋለን፤

ነፃ ስንሆን፥ "የኢትዮጵያ መሪ ምን አለ?" ተብሎ ከአፉ የሚወጣው ቃል ሲጠበቅ በአደባባይ እናያለን፤

ነፃ ስንሆን፥ በመሪያችን እንኮራለን፤

ነፃ ስንሆን፥ መሪያችንን በቲማቲምና በእንቁላል ሳይሆን በአበባና በባንዲራ እንቀበላለን፤

ነፃ ስንሆን፥ መሪያችንን ከስሰን ረትተን እንገባለን፤

ነፃ ስንሆን፥ መንግሥት ቅጥራችን፥ አገልጋያችን፥ ዘበኛች ይሆናል፤

ነፃ ስንሆን፥ መሪያችን ወስላታ ከሆነ እሱን አባርረን ሌላ መሪ እንቀጥራለን፤

ነፃ ስንሆን፥ ጓደኞቻችን ነፃዎቹ እነ ህንድ፥ እነ ስዊድን፥ እነ አሜሪካ ይሆናሉ፤

ነፃ ስንሆን፥ አገራችን ውዳቂ አገሮች ከሚባሉት አንዷ መሆኗ ይቀርልናል፤

ነፃ ስንሆን፥ በሀገራችን መበልጸግ እንጂ መሰደድና የሰው አገር ማበልጸግ ይቀርልናል፤

ነፃ ስንሆን፥ የድንጋይ ዳቦ ዘመን ባይመለስም ምጽዋት ለመቀበል እጆቹን ወደኢትዮጵያ የሚዘረጋ ይበዛል፡፡

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ፤**

እጅህ የታሰረበትን ሰንሰለት ወያኔ አይፈታልህም፡፡ አንተ ራስህ በጣጥሰህ ነፃነትክን እንድትጐናጸፍ ከአባቶችህ የወረስከው ጀግንነትህ ያስገድድሃል፡፡ ቆርጦ ለመነሣት ምንድን ነው የምትጠብቀው? የጎበዝ አውራዎች ሆይ፤ ሕዝብ እየጠራችሁ ነው፡፡ "አለንልህ፤ ተከተል" በሉት--ሳይመሽ፥ ብርሃን ሳይሸሽ፤ መለስ የባሰውን ነገር ሳያበላሽ፡፡